# የጅማ ዩኒቨርስቲ የዋናዉ ግቢ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ህብረት ሥራ ማህበር

## የውስጥ ብድር አስተዳደር ደንብ

መስከረም 2015 ዓ.ም

ጅማ

# የውስጥ ብድር መመሪያ

የጅማ ዩንቨርስቲ ዋናው ግቢ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ህብራት ስራ ማህበር ስራ አስፈፃሚ የማህበሩን የስራ እንቅስቃሴ እየገመገመ የተለያየ አሰራሮች ተግባራዊ ሲያደርግ ቆይቷል፤ ከጥቅምት 01, 2015 ዓ.ም ጀምሮ አዲስ የብድር መመሪያ ያዘጋጀ ሲሆን፤ መመሪያውም **የጅማ ዩንቨርስቲ ዋናው ግቢ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ህብራት ስራ ማህበር የውስጥ ብድር መመሪያ** 2015 ይባላል፤ ማንኛውም ብድር ጠያቂ ከጥቅምት 2015 ዓ.ም. ጀምሮ በመመሪያው መሰረት የብድር ጥያቄው ተግባራዊ ይሆናል፡፡

# የገንዘብ ቁጠባና ብድር ህብረት ሥራ ማህበር

# የዉስጥ ብድር አስተዳደር ደንብ

## 1. የማህበሩ የብድር አገልግሎት አላማ

1.1. በማህበሩ ዉስጥ የተለያዩ አይነት የብድር አሰራር ተግባራዊ በማድረግ ለአባሉ የብድር አገልግሎት በስፋት ማቅረብ

1.2. ለተለያዩ ለልማት ሥራዎች ጥቅም ሊዉል ሚችል የገንዘብ3 አቅርቦት መፍጠር፣

1.3. የብድር አጠቃቀም ልምድና ባህል ማዳበር

1.4. ለአባላት የብድር አገልግሎት በመስጠት አባላት ወደ ተሻለ ኑሮ ደረጃ በማሳደግ የአባላትን ገቢ አስተማማኝ እንዲሆን ማድረግ፣

## 2. ብድር ኮሚቴ ወይም የብድር ባለሙያ አቋም

2.1. ብድር ኮሚቴ አቋም

2.1.1. የማህበሩ ብድር አስተዳደር በማህበሩ ብድር ኮሚቴ እንዲሰራ ይደረጋል፣

2.1.2. በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ በአንቀጽ 21-22 በተቀመጠዉ መሠረት የብድር ኮሚቴ በሥራ አመራር ኮሚቴ ተመርጦ በጠቅላላ ጉባኤ እንዲፀድቅ ይደረጋል፣

2.1.3. የብድር ኮሚቴ አባላት የራሳዉን የዉስጥ የሥራ ድልድል ያደርጋሉ፣ ኮሚቴዉ ሊቀመንበር፣ ፀሐፊና አባል ወይም አባላት ይኖሩታል፣

2.1.4. ለብድር ኮሚቴ አባልነት ለመመረጥ በመተዳደሪያ ደንቡ አንቀጽ 12 እና 21 መሰረት ይሆናል፣

2.1.5. የብድር ኮሚቴ ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፣

2.1.6. የብድር ኮሚቴ የበድር ዉሳኔ ሃሳብ በሚያስተላልፍበት ወቅት በመተዳደሪያ ደንብ የተቀመጠዉ የስብሰባ ስርዓት ማክበር አለከበት፣

2.2. የብድር ባለሙያ

2.2.1. የማህበሩ ብድር አስተዳደር ስራ በብድር ባለሙያ እንዲሰራ ይደረጋል፣

2.2.2. የማህበሩ ብድር አገልግሎት በተቀላጠፈ ሁኔታ ለአባላት መስጠር እንዲያስችለዉ እንደ ስራዉ ስፋት የተወያየ የብድር ክፍል ወይም መምሪያ ያዋቅራል ወይም የብድር ባለሙያ ይቀጥራል፣

2.2.3. የብድር ባለሙያ አቀጣጠር ወይም የብድር ክፍል ወይም መምሪያ ማህበሩ የዉስጥ የሰዉ ሀይል አስተዳደርና አደረጃጀት ደንብ ይሆናል፣

## 3. የማህበሩ የብድር ኮሚቴ ወይም የብድር ባለሙያ ተግባር፣

3.1. የማበሩ የብድር ኮሚቴ ተግባር

3.1.1. የማህበሩን የዉስጥ የብድር አስተዳደር ደንብ ተግባራዊ ያደርጋል፣

3.1.2. የማህበሩ የብድር አገልግሎት የአባሉን ፍላጎት መሰረት ያደረገ መሆኑን ይከተላል፣ ያረጋግጣል፣

3.1.3. ለማህበሩ የሚቀርቡ የብድር ጥያቄዎችን በመተዳደሪያ ደንቡና በዚህ የዉስጥ የብድር አስተዳደር ደንብ መሠረት መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

3.1.4. ብድር ጠያቂዉ ለሚጠይቀዉ ብድር በቂ ዋስትና ማቅረቡንና አስፈላጊ የብድር ሰነዶች መሟላታቸዉን ያረጋግጣል፣

3.1.5. ብድሩ ከመጠየቁ በፊት ለብድር አገልግሎት የተመደበ ገንዘብ መኖሩን ያረጋግጣል፣

3.1.6. ኮሚቴዉ ዉሳኔዎችንና የአመልካቹን የግል ሁኔታዎች በሚስጥር መያዝ አለበት፣

3.1.7. የቀረበለትን የብድር ጥያቄ መርምሮ ከዉሳኔ ሃሳብ ጋር ለሥራ አመራር ኮሚቴ ያቀርባል፣

3.1.8. የተሰጠ ብድር ለተጠየቀበት ዓላማ ማዋሉን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፣

3.1.9. የተሰጠ ብድር በተቀመጠዉ የጊዜ ሰሌዳ ዉስጥ እንዲመለስ ያደርጋል፣በወቅቱ ያልተመለሰ ብድርን ያልተመለሰበትን ምክንያት ያጣራል ዉጤቱን ለሥራ አመራር ኮሚቴ በሪፖትር ያሳዉቃል፣

3.1.10. የብድር መክፈያ ጊዜ ማራዘሚያና ተጨማሪ ብድር የተጠየቀበትን ማመልከቻ መርምሮ ዉሳኔ እንዲሰጥበት ለሥራ አመራር ኮሚቴ ያቀርባል፣

3.1.11. አዳዲስ የብድር አሰራር ሃሳብ ያፈልቃል፣ ለሥራ አመራር ኮሚቴ ያቀርባል፣

3.1.12. የዉስጥ የብድር አስተዳደር ደንብ እንዲሻሻል ሃሳል ያቀርባል፣ ሲፈቀድ ይተገብራል፣

3.1.13. ስለብድር የስራ እንቅስቃሴ ቢያንስ በ30 ቀናትለሥራ አመራር ኮሚቴ ሪፖርት ያቀርባል፣

3.1.14. የብድር ኮሚቴዉ ያካበተዉን ልምድ ለተተኪ የኮሚቴ አባል ወይም የብድር ባለሙያ የማስተማርና ልምዱን የማካፈል ኣላፊነት አለበት፣

3.1.15. ስለብድር ጥያቄ አቀራረብ አሰጣጥ፣ አመላለስ አስመልክቶ እቅድ ያወጣል፣ በስራ አመራር ኮሚቴ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፣

3.1.16. የማህበሩን አመታዊ የብድር ፍላጎት መጠን ያዘጋጃል ለሥራ አመራር ኮሚቴ እንዲፈቅድ ያቀርባል፣

3.1.17. ሌሎች ብድር ነክ የሆኑ ስራዎች በማህበሩ ሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ ሲሰጡት ይተገበራል፣

## 4. የብድር ኮሚቴ ኃላፊነት ወይም የብድር ባለሙያ ኃላፊነት

### 4.1. የብድር ኮሚቴ ኃላፊነት

4.1.1. በዉስጥ የብድር አስተዳደር ደንብ ከተወሰነዉ መጠንና ጊዜ በላይ ለአንድ ተበዳሪ ብድር መስጠት በኃላፊነት ያስጠይቃል፣

4.1.2. ያለዋስትና ወይም በቂ ባልሆነ ዋስትና ብድር መስጠት በኃላፊነት ያስጠይቃል፣

## 5. የብድር ጣሪያ

5.1. አንድ አባል ሊበደር የሚችለዉ ከፍተኛ የብድር ጣሪያ ማህበሩ በየአመቱ ከሚመድበዉ የብድር ገንዘብ ዉስጥ 10 በመቶ መብለጥ የለበትም ሆኖም ግን አስገዳጅ ሁኔታዎች በሚፈጠሩ ጊዜ የብድር ጣሪያ መጠን በጠቅላላ ጉባኤ ተወስኖ ሊስተካከል ይችላል፣

5.2. በአንቀጽ 5.1 እንደተጠበቀ ሆኖ የሚፈቀደዉ የብድር መጠን ተበዳሪዉ በሚያቀርበው ዋስትና ያለው ተቀማጭ እና ወርሀዊ የመክፈል አቅም መሰረት ይሆናል፣

5.3. አንድ ተበዳሪ ብድር ማግኘት የሚችለው ከማህበሩ ውስጥ ባለው ተቀማጭ መጠን ሆኖ ይህንን ለማሳደግ በመደበኛው በየወሩ ከሚቆጥበው ውጭ ገንዘብ ገቢ ካደረገ ገቢ የተደረገው ብር ቢያንስ 3 ወር ካልሞላው ለ3 ዕጥፍ ብድር አይውልም፡፡ ገቢው ግን ብድር ሙሉ ለሙሉ ለመክፈል ከሆነ ያለውን ተቀማጭ በሌሎች ህግ መሰረት መበደር ይችላል፡፡

5.4. የብድር ጣሪያ መጠን ሊሻሻል የሚችለው ከማህበሪ አባላት ውስጥ 2/3ኛው በተገኙበት ሊወሰንና አግባብ ያለው ባለስልጠን ፍቃድ ሲያገኝ ብቻ ነው፡፡

## 6. የብድር ማመልከቻ አቀራረብ

6.1. ማህበሩ የብድር ማመልከቻ አዘጋጅቶ ያቀርባል፣

6.2. የብድር ማመልከቻ በተበዳሪዉ ተሞልቶና ተፈርሞ መቅረብ አለበት፣

6.3. የብድር ማመልከቻ ለስራ አመራር ኮሚቴ ፀሐፊ ወይም ስራ አስኪያጅ ይቀርባል፣

6.4. የስራ አመራር ኮሚቴ ወይም ስራ አስኪያጅ ማመልከቻዉን መዝግቦ ከአንድ ቀን ባልበለጠ ጊዜ ዉስጥ ለብድር ኮሚቴ ወይም ለብድር ባለሙያ ይመራል፣

6.5. የብድር ኮሚቴ ወይም የብድር ባለሙያ የተመራበትን የብድር ማመልከቻ እንደየአቀራረባቸዉ ቅደም ተከተል ተከታታይ ቁጥር በመስጠት ተራዉን እንዲጠብቅ ያደርጋል፣

6.6. በአባሉ የሚቀርብ ማመልከቻ የሚከተሉትን ማሟላት አለበት

6.6.1. የአመልካቹ ስም
6.6.2. አድራሻ
6.6.3. የብድሩ መጠን
6.6.4. ብድሩን የሚወስድበት አላማ
6.6.5. የብድር ዘመን
6.6.6. የክፍያ ጊዜ
6.6.7. የዋስትና ሁኔታና አቀራረብ

6.7. ከብድር ማመልከቻ ጋር የሚከተሉት በማስረጃነት መቅረብ አለባቸዉ፣ ብድር ኮሚቴ ወይም ባለሙያ ከብድር ማመልከቻ ጋር የቀረበዉን ማስረጃ ትክክል መሆኑን ያረጋግጣል፣

6.7.1. ቁጠባ ያለ ገንዘብ

6.7.2. የዕጣ መጠን

6.7.3. ለተበዳሪ ዋስ የሆኑ አባላት የቁጠባና የእጣ መጠን

6.7.4. የተበዳሪዉ ዋስትናና የዋስትና ማረጋገጫ

6.7.5. የተበዳሪዉ የስራ እቅድና ሌሎች ጉዳዮች

6.7.6. ተበዳሪዉ ዋስ የሆነበት ብድር ካለ የብድሩ መጠንና ያለበት ሁኔታ፣

6.7.7. ተበዳሪዉ ከማህበሩ ተበድሮ ከሆነ የብድር መጠን፣ የተበደረበት ጊዜ የተከፈለና ያልተከፈለ ብድር መጠን፣

6.8. የብድር ኮሚቴ ወይም የብድር ባለሙያ በአመልካቹ በቀረበዉ የብደር ማመልከቻ መነሻ መሰረት በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ መጠይቅ ማድረግ ይቻላል፣

6.8.1. ተበዳሪዉ የጠየቀዉ ብድር ሊያዉለዉ ከፈለገ የስራ መስክ ጋር በትክክል የሚጣጣም መሆኑን ለማወቅ፣

6.8.2. ተበዳሪዉ ብድሩን ከመዉሰዱ በፊት ስለገንዘብ አጠቃቀም ተጨማሪ ግንዛቤ መኖሩን ማረጋገጥ፣

6.8.3. አመልካቹ ያቀረበዉ የብድር ጥያቄና የሞላዉን ማመልከቻ ትክክለኛነት ማረጋገጥ፣

6.8.4. በቀረበዉ ማመልከቻ ላይ ያልተብራራና ግልፅ ያልሆኑ ጉዳዮችን ግልፅ ለማድረግ በቂ ማስረጃ መቅረቡን ማረጋገጥ፣

6.8.5. የተበዳሪዉን የኋላ ታሪክ ለማወቅ ማጣራት፣

6.8.6. በተበዳሪዉ የሚቀረበዉ ዋትና ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ፣

6.9. መጠይቁ በብድር ኮሚቴ ወይም የብድር ባለሙያዉ ተፈርሞ ከአባሉ የብድር ማመልከቻ ጋር በአባሪነት ተያይዞ በአግባቡ መቀመጥ ይኖርበታል፣

6.10. የብድር ኮሚቴዉ ወይም የብድር ባለሙያ የቀረበዉን የብድር ጥያቄ ማመልከቻ ዉሳኔ ሃሳብ በ 5 ቀናት ዉስጥ ለስራ አመራር ኮሚቴ ወይም ስራ አስኪያጅ ማቅረብ አለበት፣

7. የብድር ዘመን

7.1. አንድ አባል ብድር ማግኘት የሚችለው በመተዳደሪያ ደንቡ አንቀጽ 40 እና በዚህ የውስጥ የብድር አስተዳደር ደንብ መሰረት ይሆናል፤

7.2. የብድር ዘመን በመተዳደሪያ ደንቡ አንቀጽ 24 መሰረት ይሆናል፤

7.3. ማህበሩ የሚከተሉት የብድር ዘመን ይኖሩታል

7.3.1. የአጭር ጊዜ ብድር፡ ማለት በሁለት ዓመትና ከሁለት ዓመት በታች ባሉት ጊዜያት ውስጥ የሚመለስ ብድር ሲሆን የገንዘብ መጠኑም

ሀ. ለአስተዳደር ሰራተኛ እስከ ብር 30,000.00(ብር ሰላሳ ሺ.ህ ) ድረስ

ለ. ለመምህራን፣ ለሐኪሞች፣ ለቴክኒካል ረዳቶች እና ለፕሮጀክት ሰራተኞች እስከ ብር 50,000.00(ሀምሳ ሺ.ኅ) ድረስ ይሆናል፡፡

7.3.2. የመካከለኛ ጊዜ ብድር፡- ማለት በአምስት ዓመትና ከዓምስት ዓመት በታች ባሉት ጊዜት ውስጥ የሚመለስ ብድር ሲሆን፣ የገንዘብ መጠኑም ከ 50,001.00-300,000.00( ከሀምሳ ሺ.ህ አንድ ብር እስከ ሶስት መቶ ሺ.ኅ ብር ) ይሆናል፡፡

7.3.3. የረጅም ጊዜ ብድር፡-ማለት በሰባት ዓመትና ከሰባት ዓመት በታች ባሉት ግዜያት ውስጥ የሚመለስ የብድር ዓይነት ሲሆን የገንዘብ መጠኑም ከ300,001.00 (ከሶስት መቶ ሺ.ህ አንድ ብር) በላይ ይሆናል፡፡

7.4. ተበዳሪው ከተወሰነው የብድር ዘመን በፊት ብድሩን መክፈል ይችላል፡

7.5. ለማህበራዊ ጠቀሜታና ለግል ፍጆታ የሚሰጥ ብድር የአጭር ጊዜ ብቻ ይሆናል፤

8. የብድር ወለድ

8.1. ማህበሩ ለሚሰጠው የብድር አገልግሎት ወለድ ያስከፍላል፤

8.2. ማህበሩ ለሚሰጠው የተለያየ አይነት የብድር አገልግሎት የተለያየ የወለድ ተመን ሊኖረው ይችላል፤

8.3. የሥራ አመራር ኮሚቴ ወይንም ቦርድ የተለያየ ዓይነት የወለድ ተመን በማውጣት ተግባዊ ያደርጋል፤

8.4. ማህበሩ የወለድ ተመኑን ለማውጣት የሚከተሉትን ነጥቦች ግምት ውስጥ ማስገባት አለበት፤

8.4.1. ለብድር የሚውለው ገንዘብ እለታዊ ዋጋ

8.4.2. ብድሩን ለማስፈጸም የሚደረግ አስተዳደራዊ ወጪ

8.4.3. መመለስ ለማይችሉ ብድሮች መሸፈኛ

8.4.4. በወቅቱ የገንዘብ የመግዛት አቅም

8.4.5. ማህበሩ ማግኘት ያለበት ትርፍ

8.5. ማህበሩ የብድር ወለድ ተመኑን በገበያ በሚኖረው የፍላጎትና አቅርቦት ሁኔታ እያየ ማስተካከል ይችላል፡፡ ሆኖም ለብድር የሚመደበው የወለድ ተመን በመተዳደሪያ ደንብ ላይ ከተቀመጠው ወለድ ተመን ማነስ የለበትም፤

8.6. የብድር ወለድ ተመን መታሰብ የሚጀምረው ተበዳሪው ገንዘቡን ከተረከበበት ቀን ጀምሮ ይሆናል፤

8.7. በየጊዜው ለሚኖሩ የወለድ ተመን ለውጥ ማህበሩ ለተበዳዎች በጽሁፍ ወይንም ማስታወቂያ በመለጠፍ ያሳውቃል፤

8.8. ማህበሩ በብድር ውሉ መሰረት ከተበዳሪው ወለድና ዋና ገንዘብ ይሰበስባል፤

8.9. በውሉ መሰረት ወቅቱን ጠብቀው ለማይከፈሉ ብድሮች ማህበሩ ተጨማሪ ወለድ ያስከፍላል፡፡

9. የብድር ዋስትና

9.1. ተበዳሪው ለሚበደረው ገንዘብ ዋናውን፣ ወለዱንና ሌሎች ወጭዎችን ቸምሮ ለመክፈል የሚችል ዋስትና ማቅረብ አለበት፣

9.2. ማህበሩ ብድር በመስጠት ሊደርስ የሚችለውን ያልተጠበቀ ችግር መከላከል አለበት፣

9.3. ተበዳሪው በማህበሩ ያለውን የመደበኛ ቁጠባ ገንዘብ ለብድር አገልግሎት ሊያውለው ይችላል፣ መደበኛ ቁጠባ እንደ ዋስትና ሆኖ ያገለግላል፡

9.4. ተበዳሪው ካለው የመደበኛ ቁጠባ መጠን በላይ ብድር የሚፈልግ ከሆነ ለዚሁ ተራፊ ለሆነው ገንዘብ የሚከተሉትን በዋስትና ማቅረብ ይችላል፣

9.4.1. የማህበሩ አባል የሆነ

9.4.2. በማህበሩ ውስጥ በተለያየ ሁኔታ የተጠራቀመ ገንዘብ

9.5. ብድር ጠያቂው በተለያየ ምክንያት የሚፈለግበትን ዕዳ መክፈል ባይችል ማህበሩ አባል ካለው የመደበኛ ቁጠባ፣ የዕጣና ሌሎች የአባሉን ድርሻ ለእዳ ማካካሻ ማዋል ይችላል፣

9.6. ተበዳሪው ዕዳውን መክፈል ካልቻለ የዋሱ ቁጠባና ዕጣው ለዕዳው ማካካሻ ይውላል፣

9.7. አንድ አባል የቁጠባውን 100 በመቶ ድረስ ያለ ተጨማሪ ዋስትና ሊበደር ይችላል፣

9.8. ዋስትና ሊወርድ ወይም ሊቀየር የሚችለው በቀሪው የዕዳ መጠን ተተኪ ዋስትና ሲቀርብና ውል እንደ አዲስ ሲፈረም ወይንም ብድሩ ሲጠናቀቅ ብቻ ነው፣

9.9. አንድ አባል ቀጠባውን ለሌላ አባል በዋስትና ሊያሲይዝ የይችላል

9.10. ተበዳሪው የከፈለው የብድር ተመላሽ ገንዘብ መጠንና ቀሪው ዕዳ በተበዳሪው ዋስትና የመሚሸፈን መሆኑን ማህበሩ ካረጋገጠ ብድሩ ተከፍሎ ሳያልቅ ዋሶች ነፃ ሊሆኑ ይችላሉ፣

9.11. ለሌላ ተበዳሪ ዋስ የሆነ ብድር ጠያቂ ከዋስትና ነጻ በሆነው የገንዘብ መጠን መሰረት ብድር ሊያገኝ ይችላል፡፡

10. ማህበሩ የሚሰጣቸው የብድር አይነቶች

10.1. ለአጭር ገዜ

10.1.1. ለእለታዊ ፍጆታ

10.1.2. ለማህበራዊ አገልግሎት፡-የትምህርት ቤት ክፍያ፣ ለአነስተኛ ህክምና ወጪ …

10.2. መካከለኛ ጊዜ

10.2.1. ለገቢ ማስገኛ

10.2.2. ለቋሚ ንብረት፣ ለግብዓት፣ ለቤት ግንባታና ለተለያዩ ግዢዎች

10.2.3. ለህክምና

10.3. የረዥም ግዜ

10.3.1. የቤት መግዣ፣ የመኪና እና ሌሎችም

11. የብድር አፈቃቀድ

11.1. የብድር ኮሚቴ ወይንም የብድር ባለሙያ የሚቀርብለትን የብድር ጥያቄ ከመወሰኑ በፊት የሚከተሉትን ማጤን አለበት፣

ሀ. የተበዳሪውን አባል የግል ባህሪ፣በህብረተሰበ ውስጥ ያለው ተቀባይነት፣ የገንዘብ አጠቃቀም ልምድ ወይም ችሎታ፣የማህበሩን ህግና ደንብ አክባሪ መሆኑን፣

ለ. ተበዳሪው ብድሩን ለመጠቀም የፈለገበት ስራ

ሐ. ተበዳሪው በቋሚና ተንቀሳቃሽ ያለው ንብረት

መ. ተበዳሪው የሚያቀርበው ዋስትና ብቃት ከሚፈልገው የዋስትና መጠን ጋር ያለው ተመጣጣኝነት

ሠ. ቀደም ሲል የተሰጠው ብድር አይነትና አመላለስ ላይ ያለው ልምድ፣ በዋስትና የተያዘ ገንዘብ እንዳለ መታየት አለናቸው፡፡

11.2. ማንኛውም ብድር ከመሰጠቱ በፊት የማህበሩ የፋይናንስ ሁኔታ የሚገልጽ

11.2.1. በቁጠባ የተቀመጠ

11.2.2. ለብድር የዋለ

11.2.3. ከብድር የተሰበሰበ

11.2.4. ያልተሰበሰበ ብድር

11.2.5. ሊሰበሰብ የሚችል የመክፈያ ግዜው ያለፈበት ብድር

11.2.6. ሊሰበሰብ የማይችል የብድር መጠን፣ የሚገልጽ ሪፖርት ተዘጋጅቶ ከቀረበ በኋላና ማኀበሩ ጤናማ የፋይናነስ አቅም ላይ መሆኑን ከተረጋገጠ ብድሩ ይሰጣል፡፡

11.3. ማንኛውም ተበዳሪ የሚከተሉትን መስፈርት ካሟላ የጠየቀው ብድር ፣ ይሰጠዋል፡፡

11.3.1. አንድ ተበዳሪ ለመጀመሪያ ግዜ ብድር ለመውሰድ የብድር ጥያቄ ካቀረበ ብድሩ የሚፈቀድለት ከማህበሩ ውስጥ ለብድሩ ተመጣጣኝ ዋስ ሲያቀርብ ብቻ ነው፡፡

11.3.2. ይህ ተበዳሪ በድጋሚ ብድር ለመውሰድ ጥያቄ ቢያቀርብ ያለፈ ብድር አመላለስ ተገምግሞ ውጤታማ ከሆነ በሚያቀርበው ዋስትና መሰረት ብድሩ ሊሰጠው ይችላል፡፡

11.4. ብድር ጠያቂው በአንቀጽ19 የተጠቀሱትን አንዱን ፈፅሞ ከተገኘ ብድር ላይፈቀድለት ይችላል፡

11.5. ሆኖም ግን ብድር ጠያቂው በብድር ኮሚቴ ወይም በብድር ባለሙያ ውሳኔ ካልተስማማ ቅሬታውን በማመልከቻ ለስራ አመራር ኮሚቴ ማቅረብ ይችላል፡፡

11.6. ማህበሩ ብድር ጠያቂውን ለመገምገም የሚያስችል የብድር ጠያቂ መገምገሚያ ቅፅ ያዘጋጃል፡፡

11.7. የብድር ጠያቂ መገምገሚያ ቅጽ የሚከተሉትን ነጥቦች መያዝ ይኖርበታል፡፡

11.7.1. የማመልከቻው ቁጥርና ቀን

11.7.2. አጠቃላይ የየተበዳሪው ሁኔታ

11.7.3. የተበዳሪው ብድር የመመለስ አቅም

11.7.4. የተበዳሪው ዋስትና ሁኔታ

11.7.5. የተበዳሪው የብድር አመላለስ ሁኔታ

11.7.6. የውሳኔ ሃሳብ

11.7.7. የስራ አመራር ኮሚቴ ወይም የስራ አስኪያጅ ውሳኔ

11.8. የስራ አመራር ኮሚቴ ወይም የስራ አስኪያጅ ቀረበለትን ብድር ኮሚቴ ውሳኔ በ 5 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ መርምሮ ያፀድቃል፡፡

12. የብድር ውል

12.1. ማህበሩ ለአባላቱ ለሚሰጠው የብድር አገልግሎት የብድር ውል ቅጽ ያዘጋጃል፡፤

12.2. ተበዳሪውና ዋሱ(ዋሶች) ከማህበሩ ጋር ተዛቢዎች ባሉበት በግንባር ቀርበውይፈርማሉ፡፡

12.3. የብድር ውሉ፡ብድሩ ሚውልበት ዓላማ፤ የብድር መጠን፡ የወለድ ምጣኔ፡የዋስትና ሁናቴ፡የብድር አመላለስ፡ግዴታዎችና ኃላፊነቶች ውሉ ሚፀናበት ሁኔታ፤ የተበዳሪውንና የዋስ ስም፤አድራሻና ፊርማ፡ የአበዳሪው ስምና ፊርማ፤የታማኞች ስም አድራሻና ፊርማ፤ በግልጽ ማመልከት አለበት፤፤

12.4. የብድር ውል ከተፈፀመ በኋላ ክፍያ በአንቀጽ 13 መሰረት ይፈፀማል፡፡

12.5. የብድር ውሉ ከተበዳሪው ማመልከቻና ከብድር ኮሚቴ ውሳኔ ጋር ተያይዞ በማህበሩ ፅ/ቤት መቀመጥ አለበት፤፤በምንም ዓይነት ሁኔታ ከማህበሩ ፅ/ቤት የብድር ውሉ መውጣት የለበትም፤፤

13. ለተበዳሪዎች የብድር ገንዘብ ስለመልቀቅ

13.1. ለተበዳሪው የተፈቀደው የብድር ገንዘብ በአንድ ግዜ ወይም በየምዕራፉ መክፈል ይቻላል፤

13.2. ማህበሩ የብድር ውሳኔዎችና ውሉ ተሟልቶ በቀረበለት በ7ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ብድሩን ለተበዳሪው የመክፈል ግዴታ አለበት፤

13.3. ማህበሩ ለተበዳሪው ክፍያ የሚፈፅመው በቼክ ወይም በጥሬ ገንዘብ ወይም በኤሌክትሮኒክስ መንገድ ይሆናል፡፡

13.4. ብድሩ በየምዕራፍ ሚከፈል ከሆነ የሚቀጥለው ብድር ከመሰጠቱ በፊት ተበዳሪው ቀደም ብሎ በየምዕራፉ ለወሰደው በድር አጠቃቀም ማስረጃ ማቅረብ አለበት፡፡

13.5. ብድር የተፈቀደለት አባል በ15 ቀን ውስጥ ከአቅም በላይ ባልሆነ ምክንያት ብድሩን ካልወሰደ ወይም ሌላ ስምምነት ካላደረገ በቀር ብድሩ ይሰረዛል፤፤

13.6. ብድር ክፍያው እንደተፈፀመ በማህበሩ የሂሳብ መዝገብና ሰነዶች ውስጥ ዕዳው መመዝገብ ይኖርበታል፡፡

14. ተጨማሪ ብድር ስለመጠየቅ፤

14.1. ተጨማሪ ብድር ጥያቄ ሲቀርብ የብድር ጥያቄዉ ተገቢነት ታይቶ ተጨማሪ ብድር ሊፈቀድ ይችላል፣

14.2. ለሚቀርበዉ ተጨማሪ ብድር ጥያቄ በአዲስ መልክ የብድር ውል መያዝ አለበት፡፡

14.3. ተጨማሪ ብድር የሚፈቀደዉ ከቀድሞ ብድር ላይ 50 በመቶ በላይ የሚሆነዉ ብድር መከፈሉ ሲረጋገጥ ብቻ ነው፡፡

14.4. ተጨማሪ ብድር ጥያቄ ሊፈቀድ የሚችለዉ ከዚህ በፊት የተሰጠዉ ብድር ውጤታማ ወይም ትርፋማ በሚያደርግ ተግባር መዋሉን ከተረጋገጠና በተጨማሪነት የተጠየቀው ብድር ውጤታማ ይሆናል ተብሎ ሲታመን ብቻ ይሆናል፣

14.5. ለተጨማሪ ብድር የሚፈቀደዉ የብር መጠን ከዚህ በፊት ከነበረው ብድር ውስጥ በቀሪ እዳነት ከተመዘገበው መጠን ከ50 በመቶ ወይም ከተሰጠው ብድር ውስጥ ከ25 በመቶ መብለጥ የለበትም፣፡

15. የብድር መክፈያ ጊዜና አሰባሰብ

15.1. በብድር ወሉ ከተቀመጠዉ የብድር መክፈያ ጊዜ በፊት ተበዳሪዉ ብድሩን ከፍሎ ማጠናቀቅ ይችላል፣

15.2. እያንዳንዱ ተበዳሪ የተበደረዉን ብድር በዉሉ መሰረት ከፍሎ ማጠናቀቅ አለበት፣

15.3. ተበዳሪዉ በገባዉ ዉል መሰረት ብድሩን፣ ወለዱንና ሌሎች ግዴታዎችን ለማህበሩ ገቢ ያደርጋል፣

15.4. ማህበሩ ብድር አሰባሰብን አስመልክቶ የመሰብሰቢያ ጊዜ ሰሌዳ ሊያወጣ ይችላል፣

15.5. ተበዳሪዉ የብድር ክፍያዉን ካቋረጠ የብድር ኮሚቴ ወይም የብድር ባለሙያ ክፍያዉ የተቋረጠበት ምክንያት ለማወቅ ተበዳሪዉን በወቅቱ አቅርቦ በመጠየቅ ምክንያቱን ማጣራት አለበት፣ ስለዉሳኔዉ ለስራ አመራር ኮሚቴ ወይም ስራ አስኪያጅ ሪፖርት ማቅረብ ይኖርበታል፣

15.6. የስራ አመራር ኮሚቴ ወይም ሥራ አስኪያጁ በቀረበለት ሪፖርት በመነሳት ተበዳሪዉ ክፍያዉን የሚቀጥልበት ሁኔታ ያመቻቻል፣ ይህም ሆኖ ተበዳሪዉ ብድሩን ለመመለስ ፈቃደኛ ካልሆነ በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት አስፈላጊዉን ርምጃ ይወስዳል፣

15.7. ማህበሩ ተበዳሪዉ የተበደረዉን ገንዘብ ላለመለት አላማ አለማዋሉን ካረጋገጠ የብድር መመለሻዉ ጊዜ ሳይደርስ የወሰደዉን ብድር እንዲመልስ ያደርጋል፣

16. የብድር መክፈያ ጊዜን ሊራዘም የሚችልበት ምክንያት፣

16.1. የብድር ክፍያዉ ከተበዳሪዉ የመክፈል አቅም ጋር አለመጣጣም፣

16.2. ተበዳሪዉ ከአቅም በላይ የሆነ ተደራራቢ ችግር ሲያጋጥመዉና ይህም በበቂ ማስረጃ ሲረጋገጥ፣

16.3. የብድር መክፈያ ጊዜ ሊራዘም የሚችለዉ፣

16.3.1. ለአጭር ጊዜ ብድር ከ6 ወር መብለጥ የለበትም፣

16.3.2. ለመካከለኛ ጊዜ ብድር ከ 1 አመት መብለጥ የለበትም፣

16.3.3. ለረጅም ጊዜ ብድር ከ2 አመት መብለጥ የለበትም፣

16.4. የብድር መክፈያ ጊዜ መራዘም የሚችለዉ ቢያንስ፣

16.4.1. ለአጭር ጊዜ ብድር 50 በመቶ፣

16.4.2. ለመካከለኛና ለረጅም ጊዜ ብደር 30 በመቶ ፣ተበዳሪዉ መክፈል ሲችል ብቻ ነዉ፣

17. የብድር መክፈያ ጊዜን ስለማራዘም፣

17.1. አንድ ተበዳሪ በአንቀጽ 16 መሰረት የብድር መክፈያ ጊዜ እንዲራዘምለት በማመልከቻ ሊጠይቅ ይችላል፣

17.2. የሥራ አመራር ኮሚቴ የቀረበዉን የብድር መክፈያ ጊዜ ማራዘም ጥያቄ ከአንድ ቀን ባልበለጠ ጊዜ ለብድር ኮሚቴ አስተያየት እንዲሰጥበት ይመራል፣

17.3. የብድር ኮሚቴ የቀረበለትን የብድር መክፈያ ማራዘሚያ ጥያቄ ገምግሞ ከ7 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ የዉሳኔ ሀሳብ ለስራ አመራር ኮሚቴ ያቀርባል፣

17.4. የስራ አመራት ኮሚቴ የቀረበዉን የዉሳኔ ሀሳብ ተመልክቶ ከሶስት ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ዉስጥ ዉሳኔዉን ለተበዳሪዉ ያሳዉቃል፣

17.5. ቀደም ሲል የተገቡ ዉሎች ወይም ግዴታዎች በብድር መክፈያ ጊዜ መራዘም ምክንያት በሌላ ዉል መተካት አለባቸዉ፣

18. ስለብድር ክትትልና ቁጥጥር፤

18.1. ማህበሩ በብድር አሰጣጥና አሰባሰብ ላይ ተገቢዉን ክትትልደና ቁጥጥር ያደርጋል፣

18.2. የብድር ኮሚቴ ባለሙያዉ ለብድር ተጠቃሚ አስፈላጊዉን የሙያ እገዛ ያደርጋል፣

18.3. ለብድር አገልግሎት የሚዉለዉ ገንዘብ ከጠቅላላዉ ሀብት ከ70-80 በመቶ መብለጥ የለበትም፣

18.4. ማህበሩ የሚበደረዉ ብድር ከማህበሩ ጠቅላላ ሀብት ከ5 በመቶ መብለጥ የለበትም፣

19. ብድር የሚከለከልባቸዉ ምክንያቶች፤

19.1. በዕቅድ በአላማ ላይ ያልተመሰረተ የብድር ጥያቄ ከሆነ፣

19.2. ትክክለኛና በቂ ያልሆነ ምክንያት የሚቀርብ የብድር ጥያቄ፣

19.3. ያለበቂ ምክንያት የብድር ክፍያ ላቋረጠ ተበዳሪ፣

19.4. ከሌላ ድርጅት ወይም ግለሰብ ወይም መሰል ማህበር ገንዘብ ተበድሮ ግዴታዉን ላልተወጣ ተበዳሪ፣

19.5. ታማኝነት ለጎደለዉ ግለሰብ ፣

19.6. ቁጠባ ላቋረጠ አባል፣

19.7. ብድርን በመክፈል መልካም ሪኮርድ የሌለው አባል፣

19.8. ተበዳሪዉ ወይም ዋሱ ለሌላ አባል ዋስ ሆኖ የዋስትናዉን መጠን ወይም ቀሪዉ ዕዳ ከፍተኛ ለሆነ፣

19.9. ሌሎች መሰል ችግሮች ላለባቸዉ ተበዳሪዎች ብድር መስጠት ይከለከላል፣

20. የብድር ክፍያን ሊያስናክሉ የሚችሉ ምክንያቶች፣

የብድር ኮሚቴ ብድር እንዲሰደዋ የዉሳኔ ሀሳብ ከማቅረቡ በፊት የብድር ክፍያን ሊያሰናክሉ የሚችሉ ምክንያቶች በተገቢዉ መመርመር ይኖርበታል፣ እነዚህም፡-

20.1. ከአቅም በላይ የሆነ ብድር መፍቀድ፣
20.2. የብድር ክፍያዉ ከፍተኛ መሆን ፣
20.3. ችግር ሲያጋጥም የክፍያ ጊዜን አለማራዘም፣
20.4. በወዳጅነት የሚሰጥ ብድር፣
20.5. ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ብድር አለመመለስ (በህመም፣ በገቢ መቋረጥ ወዘተ…)፣
20.6. ግዴለሽነትና ግታዴታን መዘንጋት ፣
20.7. ገቢንና ወጪን አቻችሎ በበጀት ባለመጠቀም በሚፈጥረዉ ችግር፣
20.8. አንገብጋቢ ያልሆኑና አላስፈላጊ ብድሮች ን መፍቀድ፣
20.9. የብድር ሥ-ስርአት ሳያሟሉ የሚሰጥ ብድር፣
20.10. የተፈቀደዉ የብድር መጠን ላሰበዉ ጉዳይ በቂ አለመሆን፣
20.11. ተበዳሪዉ ታማኝ አለመሆን፣
20.12. ብድርን የመክፈል መልካም ሪኮርድ ለሌለዉ አባል መስጠት የመሳሰሉት ናቸዉ፣

21. የብድር ሰነድ አያያዝ፣

21.1. የብድር ሰነድ በጥንቃቄ መያዝ አለበት፣
21.2. ትኩረት ሊደረጉባቸዉ የሚገቡ ሰነዶች አይነት፣
21.2.1. የተበዳሪዉ ማመልከቻ
21.2.2. የብድር ኮሚቴ ዉሳኔ
21.2.3. ደጋፊ ማስረጃዎች
21.2.4. የብድር ቅጾች ፣
21.2.5. የብድር ዉል (ኮንትራት)፣
21.2.6. በብድር አጽዳቂ አካል የተፈረሙባቸዉ ሰነዶች
21.2.7. የወጪ ማዘዣዎች ፣
21.2.8. ተከፈሎ ያለቀና ገና በመክፈል ላይ ያለ ብድርን የሚያመለክቱ ሰነዶች፣
21.2.9. ሌሎች ተፈላጊ ሰነዶች፣
21.3. የብድር አገልግሎት የተፈረመባቸዉ ሰነዶች ለተተኪ ኮሚቴ አባላት በጥንቃቄና በዝርዝር ማስረከብ ይገባል ፣
21.4. ከጥንቃቄ ጉድለት የጠፉ ሰነዶች ሲያጋጥሙ በኃላፊነት ያስጠይቃል፡፣

መስከረም 2015

ዶ/ር ወሰን ለገሰ የማህበሩ ሊቀ መንበር